## <u>ውታፍ ነቃይ</u>

## ከጣሰው እንደልቡ

የኦሮሞ ብሄረተኞች በተደጋጋሚ አንዴ “በኢትዮጵያ መቃብር ላይ ኦሮሞ የምትባል ሀገር እንፈጥራለን” በሌላ ጊዜ ደግሞ “ወደ መሰረቷ ወደ 16ኛ ክፍለ ጊዜ ሄዳ በገዳ ስርዓት የምትተዳደር ኢትዮጵያ እንፈጥራለን” የሚሉንን ከቅዠት አልፎ እውን ለማድረግ የሚሰሩትን እያዬ የኢትዮጵያን ህዝብ ከእንቅልፉ የነቃ ይመስላል፡፡

እንደ ግለሰብ ጋላ ወይም ኦሮሞ የሚባል ነገድ አለ ብዬ አላምንም፡፡ የብዙዎቹ መከራከሪያ ጋለኛ ወይም ኦሮሞኛ የሚናገር ህዝብ መኖሩን የኦሮሞ ነገድ እንዳለ አድርገው ይወስዱታል፡፡ ለዚህ አጭሩ መልሴ የኦሮሞን ወይም የጋላን ታሪክ ለአጠኑ ልሂቃን ልተወው ብልም፣ ቢያንስ የእኔ ቢጤው ግን - “ኢትዮፓትሪዎት ድህረገጽ” ገብቶ የአባ ባህሪን “ዜናሁ ለጋላን” መጽሀፍ እና በታሪክ ትምህርት እውቅና ያላቸውን ሊሂቃን መጽሀፎች ሲያነብ ይገባል ባይ ነኝ፡፡ ዛሬ ጋለኛ ወይም ኦሮሞኛ ተናጋሪ የሆነው ህዝብ ትናት ሌላ ቋንቋ ተናጋሪ የነበረና ተገዶ ነፍሱን ለማትረፍ ኦሮሞኛ ተናጋሪ የሆነ መሆኑን የታሪክ መዛግብት ይመሰክራሉ፡፡

ነገሬን ለማሳጠር፣ መንግስቱ ለማ “ስልቻ ቀልቀሎ - ቀልቀሎ ስልቻ” እንዳሉት የኦሮሞን ህዝብ ከኢትዮጵያ ህዝብ ለይቶ አንድ ነገድ የሚያደርገው ምንም ታሪካዊም ሆነ ነባራዊ እውነታ የለም ብል ከእውነት የራቅሁ አይመስለኝም፡፡ በአጠቃላይ ጋላ ወይም ኦሮሞ የሚባል ነገድም ሆነ ብሄር አለ የሚሉ ካሉ፣ በተቃራኒው ከሚያምኑ ጋር የመሟገቻ መድረክ በማዘጋጀት እንተባበራለን፡፡ በሙግቶች መካከል እውነት ነጥራ ትወጣለች የሚል እምነት አለን፡፡ ለሁሉም ነገር መንግስቱ ለማ

አማራ ጊሚራ፣ ቢባልም ሻንቅላ

ሱማሌ ኪኩዩ፣ ሱዋሂሊ ባነቱ

ኩኑኑሉሉ ማሳይ፣ ኔግሮ ባማንዷቱ

ማለት እንደሆነ፣ ስልቻ ቀልቀሎ

ቀልቀሎ ስለቻ፣ ስልቻ ቀልቀሎ

ስልቻ ስልቻ፣ ቀልቀሎ ቀልቀሎ

ሌላው በአማራው ህዝብ ላይ የተፈጠረው የመካድ ስሜት ነው፡፡ በተለይ ፊደል ከመቁጠር አልፈው የተማሩ ናቸው ከሚባሉት ሳይቀር ተከድቻለሁ ቢል “ለምን እንዲህ ተሰማህ?” ለማለት አንደፍርም፡፡ ምክንያቱም መሬት ላይ ፈጦ የሚታዬው ሀቅ መካዱን የሚመሰክር ነው፡፡

ይሄን ሀቅ መረዳትና እውነቱን መቀበል ግድ ይላል፣ ምክንያቱም፣ ይሄ “ኢትዮጵያዊ ነኝ” የሚለው በተግባር ግን ከአለው መንግስት ጋር የሚተባበረው ሆዳምና ውታፍ ነቃይ ብሶቱን እንኳ ሲያሰማለት አልታይም፡፡ ኦህዴድ በሚያዝዘው ኦነግ ሸኔ ሰው በብሄሩና በሃይማኖቱ ተነጥሎ ሲታረድና ሲፈናቀል የትኛው ሙሁር ነኝ ባይ ነው የጮከለት?፣ እንድ ከተማ ሲነድና አመድ ሲሆን ማን ደረሰለት?

ለትምህርት የላካቸው ልጆቹ ታፍነው ወሬያቸው የውሃ ሽታ ሆኖ ሲቀር ማን አቤት አለለት? በአብይ የአስተዳደር ዘመን በአማራው ህዝብ ላይ ያልደረሰ ግፍ የለም፡፡ ግን የትኛውም ምሁር ወይም ሊሂቅ ነው የሚባል ከከንፈር መምጠጥ ያለፈ ደፍሮ "ይህ መሆን የለበትም?" ያለ አልታዬም፡ እንዲያውም ለክህደታቸው መሸፈኛ ሲጠቀሙበት የሚሰማው "ኢትዮጵያዊ ነኛ" የሚል የቂል አይሉት የብልጥ ንግግር ነው፡፡ ስለዚህ የአማራው ህዝብ ተክጃለሁ የሚል ስሜት ቢሰማው ትክክል ነው፣ ከገዳዮቹ ከእነ አብይ አህመድ አሊ ወግነው ከድተውታል፡፡ በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው፣ መንግስቱ ለማ "መድፌ ትሰራለህ" በሚለው ግጥሙ፣ ይህ ተማረ የሚባለው ሁሉ የዛሬ ክህደቱ ነገ በህልሙም ሳይቀር እንደሚአቃዠው ነው፡፡

ያገሬ ባላገር የተማረን ሰው፣

ከአውሮፓ ሲመለስ ሊመራመረው

መድፌ ትሰራለህ ይለዋል እያሉ፣ ያጫውቱኝ ነበር ማቹ ዶክተር ከንፉ፣

እሄድ ይመስለኛል - በአንድ አውራ ጉዳና

ቁልቁለቱን ይዤ - ከእንጦጦ ቀበና

ባላገርና እኔ - አወይ መከራ እዳ፣

ፊት ለፊት ተጋጨን - ድንገት ስንነዳ

ቸብሮሌቴን እኔ - እሱ አህያውን፣

ምንስ ሊጠይቀኝ - ምን ሊለኝ ይሆን

ከእግር እስከ ራሴ - ቢመለከተኝ፣

መድፌ ትሰራለህ? - የመጣ መሰሎኝ

ተመኘሁ በልቤ - ቢቆረጥ ምላሱ

በጥፊት ያለቀ - ድሪቶ ነው ልብሱ

ነገ የአማራው ህዝብ "ስታረድ፣ ስፈናቀል፣ ሀብት ንብረቴ ሲወድም" ምን አደረግህልኝ?" ብሎ መጠየቁ አና እንደ "መድፌ ትሰራለህ?" ጥያቄ፣ ምሁርና ልሂቅ ነኝ ባዩን ማስበርገጉ አይቀርም፡፡

ከዚህም ተጨማሪ፣ እነሱ "ኦሮሚያ የምትባል ሀገር የምንፈጥረው በኢትዮጵያ መቃብር ላይ ነው" ብለው ግልጽ ሆነው እየነገሩትና በድርጊትም እንደሚፈጽሙት፣ በወለጋ እያረዱ፣ በደቡብ ሰው ዘቅዝቀው እየሰቀሉ፣ በሲዳማ፣ በአፋር፣ በኢትዮጵያ ሱማሌ ወዘተ ሰው እያገቱ፣ ንብረት እየዘረፉና እያቃጠሉ እጅን አጣምሮ "ኢትዮጵያዊ ነኝ" ማለት ከነፍሰ ገዳዩና ከፋሽስቱ ከአብይ አህመድ አሊ ጋር ከማበር ተለይቶ አይታይም፡፡ እንዲያውም

ጠላትማ ምን ጊዜም ጠላት ነው

አስቀድሞ ማጥራት አሾክሻኪውን ነው፡፡ እንደሚባለው

ማስወገድ የሚገባው እነዚህ በኢትዮጵያዊነት ስም የሚሸቅጡ አድረባይና ከርሳሞችን መሆን አለበት የሚለው የብዙዎቹ እምነት ሆኗል፡፡ ስህተቱ ፕሮፌሰር፣ ዶክተር ወዘተ ለሚባሉት ህዝብ የሚሰጠው የተዛባ መረዳት ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ማእረጎች በአንድ ሞያ በመሰልጠን የሚገኝ ማእረግ እንጂ አዋቂነትን አያሳይም፡፡ የአሜሪካው ፕሬዜዳንት woodrow wilson በህገመንግስት ጥናት ፕሮፌሰር ነበር፣ ግን በሀገር መሪነቱ ደግሞ ደካማው ፕሬዜዳንት ነበር፣ አብርሃም ሊንከን ይህ ነው የሚባል የትምህርት ደረጃ አልነበረም፣ ግን ስሙን ተክሎ ያለፈ ትልቅ መሪ ነበር፡፡ ዊንስትን ቸርችል የክፍሉ የመጨረሻ ደደብ ተማሪ የተባለ ነበር፡፡ እንዲያውም "ስእል እንደ ጊዜ ማሳለፊያዬ" painting as pastime በሚለው መጽሀፉ ላይ መሰለኝ ያነበብሁት፣ በአመቱ መጨረሻ ተማሪዎቹ በአመጡት ውጤት መሰረት ተሰልፈው የምስክር ወረቀት ሲቀበሉ የአባቱ ማፈሪያ እስኪሆን ድረስ መጨረሻ ላይ የተሰለፈው እሱ ነበር፡፡ ግን ዊንስተን ቸርችል ትልቅ ፖለቲከኛ ለመሆኑ መስካሪ አያስፈልገውም፡፡ እና የእኛዎቹ ምሁራን፣ ልሂቃን የሚባሉት ለሆዳምነትና ለውታፍ ነቃይነታቸው መሸፈኛ "ኢትዮጵያዊ ነኝ" ሲሉ፣ አንድ ወዳጄ እንደሚለው ባያቅለሸልሹኝም፣ የተማሩትን ለኢትዮጵያ ህዝብ ህልውና፣ አንድነትና ሰላም እስካላዋሉት ድረስ ምኑ ላይ ነው? ትምህርታቸው ያሰኛል፡፡

አቶ ሽመልስ አብዴሳ - የኦህዲዶችና የኦሮሞ ብሄረተኞች ዋና አላማ ኢትዮጵያን ወደ ኦሪጅኑዋ ወደ 16ኛ ክፍለ ዘመን የገዳ ስርዓት መመለስ እንደሆነ ነግረውናል፣ ለዚህም የኢትዮጵያን የታሪክም ሆነ የባህል ቅርስ እንዲሁም ለዚህ ስራቸው እንቅፋት ይሆነናል ብለው ያሰቡትን ሰሜን ኢትዮጵያን በተለይ ደግሞ የአማራውን ህዝብ ማጥፋት ተቀዳሚ ስራቸው አድርገው ይዘውታል፡፡ ህሌናውን ዳኛ ያደረገ ሰው በዚች አንድ ወር ውስጥ ብቻ የሰሩትን ሴራ ገምግሞ ይፍረድ፣ በሃይማኖት ምክንያት ግጭታ መፍጠር፣ በሸልማት ስም ፋኖን የመከፋፈል ሙከራ፣ የአማራን ህዝብ እርስበርስ ከማጋጨት አልፎ የኦሮሞን ልዩ ሃይል - የአማራን ልዩ ሀይል ልብስ አልብሶ በአማራ ህዝብ ላይ ወረራ መፈጸም፣ ብሄር ተኮር የሆነ ጋዜጠኞችንና ማህበረሰብ አንቂዎችን ማሰር፣ ህግ አክባሪው ህዝብ ላይ ህግ ማስከበር በሚል ስም በአማራ ህዝብ ላይ ጦርነት መክፈት፣ ከሶስት አመት ልጅ ማገት እስከ 13 ዓመት ልጅ መግደል፣ ወዘተ፡፡ እንግዲህ ይሁ ሁሉ መጠነ ሰፊ ጭፍጨፋና ሴራ በአማራ ህዝብና ክልል ላይ የሚፈጸመው እነሱ ደጋግመው እንደነገሩን "ኢትዮጵያን ወደ መሰረቷ ወደ 16ኛው ክፍለ ዘመን ወስዶ፣ ኦሮሞ የሆነች በገዳ ስርዓት የምትተዳደር ሀገር ለመፍጠር" ይሄ ካልተሳካ "በኢትዮጵያን መቃብር ላይ ኦሮሚያ የምትባል ሀገር ለመፍጠር" ነው ብለውናል፡፡ ይህ እኔ የፈጠርሁት ሳይሆን ማንም ውታፍ ነቃይ የማያስተባብለው የኦሮሞ ጥንፈኞች ደግመው ደጋግመው የነገሩን መሆኑን በኢንተርኔት ገብቶ ማዬት ነው፡፡

ጽሁፌን ለመቋጨት፣ የኦሮሞ ጥንፈኞች የመጨረሻ ግባቸው በገዳ ስርዓት የምትገዛ ሀገር ለመፍጠር ከሆነ "ጨው ለራስህ ብትል ጣፍጥ" እንደሚባለው ፣ ከ20 በላይ ነገዶችን ያጠፋውን የጋላ ወረራ ታሪክ ወደኋላ ሄዶ በማንበብ ሁሉም ለህልውናው ሊቆም ይገባል እላለሁ፡፡